ቀን 9/01/2017 ዓ.ም

# አስቸኳይ ማስታወቂያ

**<u>የወላይታ ሊቃ አረካ ትም/ት ቤት በ2017 ዓ.ም የትም/ት ቤቱን መግቢያ መስፈርት የሚያሟሉ ተማሪዎችን ተቀብሎ ለማስተማር ይፈልጋል!</u>**

የወላይታ ሊቃ ትም/ት ቤት በሶዶ ማዕከል ካለው ዋና ግቢ በተጨማሪ የህዝብን ጥያቄ መሠረት በማድረግ በአረካ ከተማ ወላይታ ሊቃ ትም/ት ቤትን በ2017 ዓ.ም ትም/ት ዘመን 7ኛ ክፍል ተማሪዎችን ብቻ በመቀበል በሚቀጥሉት ዓመታት ክፍሎችን እየጨመረ ለመሄድ ለዘንድሮ በአረካ ከተማና አጎራባች ወረዳዎች(ቦሎሶ ሶሬ፣ዳሞት ፑላሳ፣ቦሎሶ ቦምቤ፣ዳሞት ሶሬ እና ከለሎች በድጋፍና ወጪ በመጋራት የሚማሩ /ከፋይ/ ተማሪዎችን በ7ኛ ክፍል አወዳድሮ ተቀብሎ ማስተማር ይፈልጋል፡፡ ትም/ት ቤቱ የሚቀበላቸው ተማሪዎች የትም/ት ቤቱን የቅበላ መስፈርት የሚያሟሉ/ፈተናውን ያለፉ) ብቻ ይሆናሉ፡፡

**<u>የተማሪ ቅበላ የሚደረግባቸው ክፍል</u>**

7ኛ ክፍል (ከ6ኛ ወደ 7ኛ) የ2016 ዓ.ም 6ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና ያለፉ ሲሆን ለፈተና ምልመላ የሚካሄድበት ውጤት በ2015 እና 2016 ዓ.ም ክፍል የሁለቱ ተከታታይ ዓመታት የክፍል አማካይ ውጤት ማለትም (የ5ኛ እና 6ኛ ክፍል) ወንድ- 80 እና ከዛ በላይ ሴት- 75 እና ከዛ በላይ ያስመዘገቡት ናቸው፡፡

- **የምዝገባ ጊዜ ፡-** ከመስከረም 13-16/2017 ዓ.ም
- **የምዝገባ ቦታ ፡- በወላይታ ልማት ማህበር አረካ ሊቃ ትም/ት ግቢ ይሆናል**
- **መግቢያ ፈተና የሚሰጥበት ቀን ፡-** መስከረም 28/01/2017 ዓ.ም **በአረካ ወላይታ ሊቃ ትም/ት ግቢ (በዕለተ ማክሰኞ) ይሆናል፡፡**
- በወልማ የትም/ት ቁሳቁስና ተያያዥ ድጋፍ የሚደረግላቸው ተማሪዎች ከቀበሌው ፍርድ ሸንጎ የተሰጠውን ድጋፍ እና ከወረዳው አስ/ር ጽ/ቤት የተሰጠውን የድጋፍ ደብዳቤ **የመግቢያ ፈተና ካለፉ በኋላ** ለወላይታ ሊቃ አረካ ትም/ት ቤት በአካል ቀርበው ማስረከብ አለባቸው፡፡

- የፈተና ዝግጅት የሚደረግባቸው ትም/ት ዓይነቶች በአዲሱ ትም/ት ፖሊሲ መሠረት ሆኖ ለ7ኛ ክፍል (ከ6ኛ ክፍል) ሀሳብ፣እንግልዘኛ እና አከባቢ ሳይንስ ሲሆን (ከእንግልዘኛ ውጭ ሀሳብና አከባቢ ሳይንስ ትም/ቶች መግቢያ ፈተና በአማርኛ እና በወላይተኛ ቋንቋ የሚዘጋጅ ይሆናል)፡፡ ሆኖም በአማርኛ ቋንቋ የሚፈተኑ ተማሪዎች በምዝገባ ወቅት ለመዝጋቢዎች የማሳወቅ ግዴታ አለባቸው፡፡

## ልዩ ማሳሰቢያ

- ትም/ት ቤቱ ለጊዜው አዳሪ ትም/ት ቤት ባለመሆኑ በትም/ት ቤቱ ለመማር የሚመዘገብ ማንኛውም ተማሪ የድጋፍ ተማሪን ጨምሮ የቀለብና የመኖሪያ ቤትን ራሱ/የተማሪው በተሰብ/የሚችል ይሆናል፡፡ ሆኖም ልማት ማህበሩ ለድጋፍ ተማሪዎች ሙሉ የትም/ት ቁሳቁስን፣ዩኒፎርምንና ለሎች ተያያዥ ነገሮችን /ከቀለብና ቤት/ ውጭ በመስጠት ያስተምራል፡፡
- ከላይ ከተጠቀሰው ክፍል ውጭ የተማሪ ቅበላ አይካሄድም ፡፡
- ያቋረጠና የደገመ ተማሪ ቅበላ አይኖርም፡፡
- ፈተናው በሁሉም ፈተና ጣቢያዎች ከጧቱ 3:00 ሰዓት ይጀምራል፤ፈተና ተጀምሮ ከ30 ደቂቃ በኋላ ወደ ፈተና ክፍል መግባት ፈጽሞ የተከለከለ ነው፡፡
- ትም/ት ጽ/ቤቶች እና የወልማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አስተባባሪዎች ከትም/ት ቤቱ ጋር በመሆን የፈተናውን ሂደት የማስተባባር ኃላፊነት አለባቸው፡፡
- የፈተና ውጤት ይፋ የሚሆነው ፈተና ከተሰጠበት ቀን በኋላ ባሉት እስከ 5 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ይሆናል፡፡
- የፈተና ውጤት ይፋ የሚሆነው በአረካ ወላይታ ሊቃ ትም/ት ግቢ ይሆናል፡፡

Wolaitta Worqqaa Mayzzana!!

ለበለጠ መረጃ 0916881178 ደውለው ማረጋገጥ ይችላሉ፡፡